## በንግግርም ይሁን ከልብ አሁን የተገኘው ‘’ኢትዮጵያ’’ የሚል ከፍታ እንዴት መጣ?

መቼስ የሰሞኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዳይናሚዝም እጅግ አስደናቂ ነው። በአጭሩ እይታችን ኢትዮጵያ የሚለው አስተሳሰብ ጎልቶ የወጣበት በርካታ ወጣ ያሉ አስተሳሰቦችና ጸረ ኢትዮጵያ አመለካከቶች የተሸፈኑበት ስደተኛው አገሩ ለመግባት ያለዉን ናፍቆት ያሳየበት  እጅግ መሳጭ ትርኢት ነበር። የታማኘን በዶክተር አብይ ፊት ተደፍቶ አክብሮቱን የገለጸበት ኢሞሽናል ትእይንት ላየ ይህ ሰው የኢህአዴግን ገመና ለማጋለጥ ለበርካታ ጊዜ ያደርገው የነበረውን በቪድዮ የታገዘ መረጃ ማቅረቡን ይጠራጥራል። አበበ ገላውም በዓለም ዙሪያ በቀጥታ ይሰራጭ በነበረ አለማቀፋዊ ስብስባ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊን ባዋረደበትና ባስደነገጠበት አንደበቱ ዶክተር አብይን አሞካሽቶበታል። ኢትዮጵያውያን ባጠቃላይ ረጋ ያለ  ወይም የተንቀራፈፈ አመለካከት ያለው እስከማይመስል ድረስ ሆ ብለን ድክተሩን ሰማይ ጥግ አድርሰናቸዋል። አንድ እውነት ግን መረዳት አያዳግትም ።

ኢትዮጵያ ብሎ የተነሳ ምን ጊዜም ቢሆን የአብዛኛውን ቀልብ መሳቡ አይቀርም። ዘረኛና ቡድንተኛ ብሆን ኖሮ ዶክተሩን  ከመጀመሪያው ደጋፊ መሆን ነበረብኝ። ምክን ያቱም  ሰውየው የመጡት ለአመታት እግዚአብሄርን ከማመልክበት ቤተ ክርስቲያን በመምጣታቸው ነው። ሆኖም ብዙ የሚያስጨንቁኝ ነገሮች አሉ። በተለይም የአገራችን ፖለቲካ ውስብስብነቱ ከበስተጀርባ የሚከተሉትን እውነታዎች መካድ እንዳልችል የተሻለ ግንዛቤ ያለኝ ይምስለኛል። ዶክተር ማሙሻ ፋንታ የሚባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪ በኢንጅነር ስመኘው ግድያ የተሰማቸውን ሃዘን ሲገልጹ በቁጭት ኧረ ሞት በቃ የሚል ምልእክት አስተላልፈዋል። በዚህ ቁጭት የተሞላበት መልእታቸው አሁን ያገኘነው ሰላም ፣ወጥቶ መግባት መቻል እረፍታችን በስንት ጣር የመጣ ዋጋ የተከፈለበት ነው። እኛ አሁን ይህ አልተመለሰም  ይህ አልሆነም በማለት ለግዝርየስ ጥያቄ የምንጠይቅበት ጊዜ ላይ አይደለንም። ግድያን መልመድ የለብንም  በማለት በምሬት ተናገሩ። እኚህ ሰው ያንገበገባቸው የሰላም መታጣት ሰዎች በወጡበት መቅረትና አሁን የተገኘውን ሰላም በማክበር እንዴት መጠበቅ እንደሚገባ ነው። በጣም ተረድቻቸዋለሁ። አዲስ አበባ ግድያ ነበር ዩናይትድ ስቴት ስ ደግሞ የፍቅርና የአንድነት ስብከት።የዋሽንግተን  ከንቲባ የኢትዮጵያውያን ቀን በማለት መወጃቸው ደግሞ ልላ አስገራሚ ትርዒት ነበር። በአገር ቤት የተምታታው የህውሀት አቋም ፣ በኢንጅነር ስመኘው ቀብርለመገኘት በወጡ ዜጎች ላይ የፖሊስ አስለቃሽ ጋዝ መተኮስ፤ በሰሜን ጎንደር የሞቱ ዳኞችን ለምቅበር የዎጣው ህዝብ ጥላት በሚለው ቡድን ላይ የያዘው ቂምና ለጥይት አይበገሬነቱን ያሳየበት ትርዒት የብዐዴን የቢሮ ሓላፊና የክልሉም የኢህ አዴግም ማእክላዊ ኮሚቴ አባል የነበሩትንና ከምር ጅግና ብለው ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያወድሷቸው አቶ ተስፋይ ሞት

አቶ ልድቱ ከህወሃት በፊት የሞቱ ቢሆንም አሁንም በህወሃት መንደር አሪፍ የፖለቲካ ሌክተር ሲሰጡና በርካታ ነባር የህወሃት መሪዎች ቁጭ ብለው ሲማሩና ኖት ሲዎስዱ ተመልክተናል። አቶ ልደቱም አላቸ ሁኮ የሚ ል ማጽናኛቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ያለ እናንተ መኖር አንችልም ብለዋቸዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ በመቀሌው ስብሰባ ከአመታት በፊት  መ ዐ ሕድን በማፍረስ  ፕሮፌሰር አስራትን  ያስገደሉበትን ተልእኮ አሁን ደግሞ አብን በማፍረስ ዶክተር ደሳለኝን ለማስገደል ሙሉ ሚሽን ተሰጥቷቸው በቅርቡ ወደ ቆራጥ አመራራቸው የሚመለሱ ይመስላል።ለማንኛውም አሁን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወደ ዶክተር አብይ ያዘነበለ ይመስላል። በርካታና በርካታ ጥያቄዎች ግን አልተመለሱም። ዶክተር ማሙሻ የቅንጦት ጥያቄ እንድሉት ግን አይደለም። የህልውና፤ የእኩልነት፤ የፍት ህና የዲሞክራሲ ጥያቄወች አልተመለሱም። የብዙዎችን ስሜት ልጎዳ እንደምችል ባውቅም በዋናነት ህወሃትንና የትግራይን ህዝብ ለያይተን ማየት አለብን። አወ ህወሃት በማንኛዉም መልኩ ለህልውናው የትግራይን ህዝብ ይጠቀማል። ህዎሃትና የትግራይ ህዝብ አንድ ነውበማለትም ፕሮፓጋንዳውን ይነዛል። ነገር ግን የትግራይ ህዝብና አንድ ፓርቲ በምንም መስፈርት አንድ ሊሆን አይችለም። ሁለተኛውና ጉንጭ አልፋ የሆነው ስብከት ላለፉት ፪፯ አመትና ከዚያም በላይ የተቀነቀነው አማራ ራሱን ለመከላከል ለምን ይደራጃል የሚል በተንኮል የታጀበ ውትወታ ነው። የአንድነት ሀይል ነኝ የሚለው አዛኝ ቅቤ አንጓች ቡድን ትችቱ ለምን ሲዳማ የደራጃል ?ለምን ኦሮሞ የደራጃል ? ለምን አፋር ይደራጃል? ለምን ትግራይ ይደራጃል ?ወዘተርፈ አይደለም ዋናው ጥያቄው ለምን አማራ ይደራጃል ?የሚል ነው።ኢትዮጵያ የሚለው ሃሳብ አሁን ለምን ገነነ?ለምንስ አብዛኛው ስሜቱን ኢትዮጵያዊ ሲባል መቆጣጠር ያቅተውል ?አሸናፊ ሆኖስ ለምን ወጣ?ድፍን ሶስት አመት በአመጽ የተናጠችው አገራችን  ’’ ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው’’ ሲባል ለምን ጸጥ አለ?ዛሬ ዶክተር አብይ አፋቸውን

ሲከፍቱና ኢትዮጵያ፤ ከሶስት ሺህ አመት በላይ እድሜ ያላት ፤ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ሲሉ ሁሉም የሚንበረከክላቸው ለምንድነው?በጣም የምወዳትና የማከብራት አንዲት እህት እንደምትረዳኝም የማልጠራጥራት ይህች ወጣትና የተማረች ሴት ከሰሞኑ ስለ አማራ ሞትና ስደት ለመሞነጫጨር ስሞክር በጣም ተቆጣች። ማስረጃህን በማለትም አንዳንድ ግድያዎች አማራን ከማሳደድና ከማጥፋት ጋር የተያያዙ ናቸው በማለቴ  ሞገተችኝ። አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገች በመሆኗና አውሮጳውያን ኢትዮጵያን ለማፍረስ አማራውን መምታት የሚለዉን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ጀምሮ የነበረውንና ያለውን ስትራቴጂ ላስረዳት አልሞከርኩም። በዚህ ረገድ በርካታ በአውሮፓውያን የተጻፉ ጸረ አማራ መጽሃፎች እንዳሉም ልነግራትና ላስረዳት አልሞከርኩም ። ምክንያቱም በመጀመሪያ በፍጹም ቅንነትና ያለ እውቀት በሆነ ልብ ስለተከራከረችኝ በሁለተኛ ደረጃ ለምን አማራ አማራ ትላለህ  በየአካባቢው  ስለተፈናቀሉ ፤ በሲዳማና ወላይታ ፣ በኦሮሞና ሶማሊያ በወልዲያና በሌሎችም አካባቢዎች ስለተፈጠሩ ግጭቶች ለምን አትጽፍም በማለት ሞገተችኝ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ባትቀየመኝ ደስ ባለኝ ነበር ፤ ነገር ግን ያየችው  ውጤቱንና ስትራቴጅውን ነው ምንጩንና ለምንስ የነገድ ክልል በአገራችን ተግባራዊ እንደሆነ፤ኢትዮጵያን ለማጥፋት አማራን ማጥፋት ስለሚለው ምእራብ ተጠንስሶ በእኛው ልጆች እየተከወነ ስላለው አተገባበር ምንም የተረዳች ስላልመሰለኝ አንዲት ጥያቄ ብቻ ጠየቅኋትና የፈለገችውን ሁሉ በማለት ስሜቷን እንድትገልጽ መመላለስ ቀጠልኩ ።

ጥያቄየም ለምን ይመስልሻል ምእራባውያን ኢትዮጵያን በ 2030 ፌይልድ ስቴት ብለው ሪፖርት ያደረጉት አልኳት። ለማንኛውም እውነታው ከዚህም የመረረ ነው። ለዚህ ነው መሰረታዊ ጥያቄዎችን ዶክተር አብይ በዘለሏቸው ቁጥር እጅግ የሚያሳስበኝ። አማራ ራሱን ለማዳን የሚያደርገውን ትግል ከመቸዉም  ጊዜ ይልቅ የምንደግፍበት ምክንያትም የምንወዳትን ኢትዮጵያ ከመጠበቅ አንጻር ነው።  አማራውን እንዴት ማጥፋት እንደሚቻል ከመዘርዘር ይልቅ ኢትዮጵያን ለማፍረስ  ምን አይነት ስትራቴጅ እንደተቀየሰ ስንረዳ ያኔ ቀጥታ ለትግሉ አጋዥ መሆን እንችላለን። ቴዎድሮስ ጸጋየ የጠየቃቸው ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ለዶክተር አብይ እጅግ ፈታኝ እንደሆኑ እረዳለሁ። ዶክተር አብይም በትክክል አድሬስ ማድረግ ቢያስቸግራቸውም ስትራቴጅካዊ ጥያቀዎች እንደሆኑ አምነዋል። ከዚህ በተጨማሪ ግን አማራው ስለተደረገበት ነጥሎ የማጥቃት ርምጃ፣ የዘር ማጽዳት ዘመቻና መዋቅራዊ ማግለል የተነሳውን ጥያቄ ችላ ያሉበት መንገድ አሳስቦኛል። ከአርባ ጉጉ  እስከ ጨለንቆ፤ ከአሶሳ እስከ ነቀምቴ ፤ ከአርሲ እስከ ባሌ፤ ከጉራፈርዳ እስከ አምቦ ከኤርትራ እስከ ትግራይ  በ አጠቃላይ የተደረገውን ስይለንት ጄኖሳይድ ከእርሳቸው በተሻለ የሚያዉቀው የለምናህወሃትን በማውገዝ ተጠምደን መሰረታዊና ወሳኝ ኩነቶችን መዘንጋት የለብንም። እርቁ እውነተኛ እንዲሆን ካስፈለገ የነበረው አማራን የማግለል መንግስታዊና መዋቅራዊ ሲስተም በግልጽ ይቅርታ ሊጠየቅበትና ልቆምምይገባዋል። በሃገራችን እውነት ነው ኦሮሞ ተገድሏል፣አውነት ነው ሲዳማው ተገድሏል፣ ትግሬው፣ ወላይታው፣ ጋሞው፣ አፋሩ፣ ቤንሻንጉሉ ፣ ሶማሊው ወዘተ  ተገሏል።በማንነቱ የተሰደበ፤ የተዋረደ፤ የተገደለና የተሳደደ ግን ከአማራ ውጪ የለም። የትኛውም ቅን የሆነ ሰው ምርምር መስራት ይችላል። ለምንድነው አብዛኛው ስደተኛ አማራ የሆነው? ለምንድነው አብዛኛው እስረኛ በማንነቱ የተገረፈው? በርካታ ለጆሮ የሚዘገንኑ ድርጊቶች የተፈጸሙበት?እነዚህን እውነታወች የሚያወጣና ፍት ህ የሚጠይቅ ዘረኛ ነው ሊባል  አይችልም። ከመሞት ለመትረፍ ከመጥፋት ለመዳን የሚደራጅ በዘርህ ተደራጀህ ተብሎ ሊዎቀስና ሊዎገዝ አይችልም። የአንድነት ሃይል ነኝ በማለት የአማራን ብሔርተኝነት ለመተቸት የሚሞክሩ ወይ ሆን ብለው የተንኮሉ ተዋናዮችናቸው አልያም በዚህ ነገድ ላይ የተደቀነው አደጋ አልታያቸውም።በቅርብ የአማራ  በሚባለው ክልል የሚኖሩ የአገው ብሔረሰብ ወጣቶች በአማራ  ህዝብ ምን ያክል ማህበረሰባዊ አልመረጋጋት ለመፍጠር እየተሞከረ  እንዳለ አጋልጠዋል። ታዋቂው የኢሳት ጋዜጠኛ  ካሳሁን በፌስ ቡክ ገጹ ለ  አማራ  ብሄርተኝነት አቀንቃኞች በማለት ለ እርምት የዘረዘራቸውን ሶስት ነገሮች አይቻቸዋለሁ።  እስኪ  እነመልከታቸው፤

'' እኛ አማራነት የሰውነት ውኃ ልክ ነው ፡ ብለን እናምናለን ''  ክርስትያን ታደለ

''ለመላዉ የአማራ ሙስሊም ወንድም እህቶቻችን በራሴና በድርጅታችን የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን)

ስም   ለወገኖቻችን ኢድ ሙባረክ ለማለት እወዳለሁ።''

ደሳለኝ ጫኔ ዳኘው

'' ሰው በተፈጥሮው ፈጣሪውን ማክበር እንዳለበት ሁሉ ኢትዮጵያም ፈጣሪዋን አማራ ማክበር አለባት''

ጋሻው መርሻ

ካስ ሽ ለምን እነዚህ አባባሎች እንዳናደዱት ብዙም አልገባኝም። ብዙውን ጊዜ አውድን ሳንገነዘብ በምናየው አባባል የምንደናገጥ ከሆነ ሌሎች በተሳሳተ መንገድ የረዱንና መበሻሸቅን ይወልዳል። ካስሽ አንድነትን የሚሰብክ የዘውግ ፖለቲካ አራማጆችን በቻለው መጠን የሚቃዎም በአብዛኛው በአዲስ አበባ አውድ ነገሮችን ስለሚያይ ከምሩ ኢትዮጵያን ደጋፊ ነው። የአማራ ብሔርተኝነት ደግሞ እንዴት እንደተወለደ ቅንጦት ፍለጋ ሳይሆን ህልውናን ለማስጠበቅ በግፊት የተፈጠረ ምናልባትም በአለም ደረጃ የመጀመሪያ በሚያሰኝ ሳይመሰረት በሚሊየን የሚቆጠር ደጋፊ ያገኘ ጎጃሜ ሆኖ ከጌጃም በመባረሩ፤ ጎንደሬ ሆኖ ከጎንደር በመባረሩ፣ ወሎየ ሆኖከወሎ የተባረረ፤ ሸዌ ሆኖ ከሸዋ የተባረረ በመንግስት ስትራክቱር ሆን ተብሎ የተገለለ መሆን የለበትም በቃኝ ብሎ የተነሳ ብሔርተኝነትነው። ከዚህ ቡድን አከሌ ይውጣልኝ አልፈልገውም የሚል የአክሌ ስፋሪ ይሄንን አድርጎብኝ እያሌ ሌሎችን ኢትዮጵያውያን የሚገፋ አይደለም። ይልቁንም በኢትዮጵያ አፈጣጠር የአንበሳውን ድርሻ ይዤ ተገፍቻለሁ ለከበር ይገባኝ ነበር በማለት እውነታውን ለመግለጽ እየሞከረ ያለ ነው። ለምሳሌ ኦሮሞ የኢትዮጵያ መስራች ነው። ስለዚህም ፈጣሪ በፍጥረቱ እንደሚከበር ሁሉ ለኢትዮጵያ አፈጣጠር የአንበሳዉን ድርሻ ወስጃለሁ ያለው ኦሮሞ ኢትዮጵያ ኦሮሞን ማክበር አለባት ቢል ክፋቱ ወይም ስህተቱ ምኑ ላይ ነው?

በኢትዮጵያ እንደሃገር መቆም ዋና ሚና የነበረው አማራ ተገልሏል፤ በአንጻሩ ግን መከበር ይገባዋል። ጋሻው መርሻ ያለዉም ይህንኑ ነው።

ሌላው የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ መሪ ይሆኑት ዶክተር ደሳለኝ ጫኔ የኢድ ሙባረክ መልእት ሲያስተላልፉ የአማራ ሙስሊም እህቶቼና ወንድሞቼ በማለት መልእታቸውን ለምን አስተላለፉ ይህ በታሪክ ተጠያቂ ያደርጋል ነው መልእክቱ። እንዴ እየመሩ ያሉት እኮ በምክን ያት የተ ቋቋመውን የ አማራ ብሄራዊ ንቅናቀ ነው ይህ በእውነቱ ያስቃል። ወግነው ያሉት አማራን ሆኖ እያለ ለምን አማራ አልክ በቅንነት ኢትዮጵያን የምትዎደው አንተ ካስ ሽ ስላልከው እንጂ ሌላ ሰው ቢለው ኖሮ የሚሰጠው ስም በፍጹም ሌላ ነበር። ወደ መጀመሪያው አባባል ልምጣ።

የሰውነት የውሃ ልክ ማለት ምን ማለት ነው። ውሃ ልክ በተለይ ህንጻ ሲሰራ የምንጠቀምበት ደረጃው ትክክልና መበላለጥ የሌለበት መሆኑን የምንለከበት መሳሪያ ነው። ከሰው ደርጃ በታች እየሆነ ያለው አማራ ከሰው እኩል ነው። አማራ ከየትኛውም ሰው አይበልጥም ከየትኛውም ሰው አያንስም። ካስፈለገ አማራ የሰውነት መለኪያ ሊሆን ይችላል መንም አይበልጠውም ማንም አያንሰውም ስለዚህ እኛ አማራነት የሰውነት ውሃ ልክ ነው ብለን እናምናለን ቢባል ምን የሚያናድድ ድና የታሪክ ተጠያቂ የሚያደርግ ነገር አለው?ለማንኛውም ሌላው የ ኢትዮጵያ ህዝብ እንዲጠራጠረው ሆን ተብሎ የሃሰት ፕሮፓጋንዳ የተነገረበት ይህ ህዝብ ላይታለልና ወደ ኋላ ለይመለስ ራሴን መከላከል ኣለብኝ ብሎ ካመረረ ሰነባበተ። በደሙ የመገንጠል ወይም ሌላ አገር የመመስረት ህልም አልነበረውም። ሌሎች አገር እንዳያፈርሱ ከኩርፊያቸው እንዲመለሱ ለበርካታ ዘመናት ሲያባብልና ራሱን ሲሰዋ ኗሯል። ዛሬም እንኳ ኢትዮጵያ የሚሉ ከፊት የተሰለፉ ሌሎች ሆነው እያለ አንድነትና ባንዲራ የሚለው አጀንዳ የአማራ ነው የቀድሞውን ስርዓት ሊጭኑብህ ነው እየተባለ በስሙ ይሰበካል። በእርግጥ የአማራ ህዝብ አንድነትን ፍቅርንና ይቅርታን አይጠላም ፤ ሰሞትለትና ሲዋረድለትም ኖሯል።

ዶክተር አብይ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማንም ያንሳቸው ማን ሊመልሷቸው ትቸግረዋል። በተለይም ቴዎድሮስ ጸጋየ የጠየቃቸው የባህርበር ባለቤት የመሆን እድል፤ በዜጎች መካከል ልዩነትን የሚፈጥረውና አንዱን ዜጋ ከሌላኛው የተለየ ጥቅም እንዲያገኝ የሚያስገድደውን ህግ እንዴት ያዩታል ሁሉም ከህገመንግስቱ ጋር የሚያያዙ መሰረታዊ ጥያቄዎች ናቸው። ይህ ብቻ ማለትም ኦሮምያ ከአዲስ አባባ ልዩ ጥቅም ታገኛለች ብቻ

ሳይሆን እንደ ቤንሻንጉል ባሉ ክልሎች ከመቶ ሰባ ሽህ በላይ የሆነው የአማራ ህዝብ ባለቤትነት ተነፍጎ ከስምንት ሺህ በታች የሆነ የህዝብ ቁጥር ያለው ባለቤት የሆነበት የክልል ህገ መንግስትም አለ። የአንድነት ሃይል ነኝ የሚለውና ትግሉን እዚህ ደረጃ አድርሻለሁ በማለት የድል አጥቢያ አርበኛ መሆን የሚዳዳው ቡድንም እነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምኑም አይደሉም። በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉና በልማት ምክን ያት የሚፈናቀሉ አርሶ አደሮች ተገቢዉን ካሳ ማግኘት ይኖርባቸዋል ፤ በየትኛውም አለም የሚሰራበት አግባብ ነው። ህገ መንግስቱ ለኦሮምያ የሰጠው ልዩ ጥቅም ግን እስካሁን ተግባራዊ ያልሆነ ለተግባራዊነቱም እጅግ ውስብስብ ህጋዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማንቆዎች የሚጠብቁት ግን ደግሞ በኦሮሚያና በሌላው  ማህበረሰብ ዘንድ ሆን ተብሎ ጥርጣሬንለማስቀመጥ የተሰራ ህገመንግስታዊ ሻጥር ነው። ሌሎችስ የፌደራል ከተሞች ለምሳሌ ድሬዳዋ አሁን ደግሞ አዋሳ ባህርዳርና መቀሌስ?ስለዚህ ዶክተር አብይ የሚሏት ኢትዮጵያ በህገመንግስቱ የለችም። ዘጎቿ የሚናፍቋትና ኢትዮጵያየ የሚሏት ውድ ሃገር ገና በዶክተር አብይ ንግ ግር ና በህዝቡ ስሜትና ተ  ስፋ ውስጥ ብቻ  ነው ያለችው።  ይህች ኢትዮጵያ ልትኖር የምትችለው መሰረታዊ ጥያቄዎች ሲመለሱ ብቻ ነው።

ሆኖም ግን በንግ ግር ደረጃም ቢሆን አሁን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለው ብዙዎችን በስሜት ፈረስ ያስጋለበው ዉጤት የመጣው በኢሳት ኢንፎርሜሽን፤በግንቦት ሰባት ትግል፤ በኦነግ ተጋድሎ አልያም በሌላ ውጫዊ ሃይል አይደለም። ኢንፎርሜሽን በተለይም እውነትን ማእከል ያደረገው መረጃ አሁን የተገኘውን ድል አምጥቷል። ይበዛም ይነስም አውነት ይሁንም ውሸት ኢሳት፤ ኦሮሞ ነትዎርክ ኣማራ ድምጽ ና ሌሎችም የ መረጃ ማእከላት አራሳቸውን አስተዋጽ ኦ አድርገዋል።በአማራ ላይ የሚነዛው የሓሰት ፕሮፓጋንዳ ደግሞ የአማራ ዎጣቶችን በማይጠበቅ ፍጥነት እውነቱን ፍለጋ ስለማንነታቸው ለማውቅ በማንነታቸው እንዲደራጁ አፋጠናቸው።

ይቀጥላል

© አዲስ ተስፋ